# በሽግግር ፍትሕ ዙሪያ ከተደረጉ የማኅበረሰብ ምክክሮች የተሰበሰቡ አበይት ግኝቶች

የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም


የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

United Nations Human Rights
OFFICE OF THE HIGH COMMISSIONER FOR HUMAN RIGHTS

የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE

# አቀራረብ /outline

- የማኅበረሰብ ምክክሮቹ መነሻ፣ አላማዎች እና አጠቃላይ ይዘት
- የማኅበረሰብ ምክክሮቹ ዋና ዋና ግኝቶች፡
    1. ሰላም እና ደኅንነት
    2. ማካካሻ
    3. እውነትን ማጣራት እና ማውጣት
    4. እርቅ እና ሰላም
    5. የወንጀል ምርመራና ክስ (ተጠያቂነት)
    6. ጥሰቶች እዳይደገሙ ዋስትና ማስቀመጥ
- ትርጉም ያለው ተሳትፎ
- የሽግግር ፍትህ ትግበራ እና ክትትል
- መደምደሚያ እና ጠቅላላ ምክረሃሳቦች

# መነሻ

**<u>የኢሰመኮ እና የተ.መ. ድ. የጋራ ምርመራ</u>**

- የሁለቱ ተቋማት የጋራ ምርመራ ቡድን በትግራይ ክልል የተፈጠረውን ግጭት ተከትሎ ተፈጽመዋል የተባሉ ጥሰቶችን በተመለከተ በጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም. ይፋ ባደረጉት የምርመራ ሪፖርት ውስጥ የሽግግር ፍትህን አስፈላጊነት አስመልክቶ የተሰጡ ምክረሃሳቦች፡
  - ***<u>ለኢትዮጵያ መንግስት</u>***፡ በትግራይ ግጭት እንዲሁም በፊት ለተፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂነትን ማስፈንን ጨምሮ "የሰብአዊ መብቶች መርሆችን የሚያሟላ፣ ሁሉን አቀፍ እና ተጎጂዎችን ማዕከል ያደረገ የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት እንዲያቋቁም;"
  - ***<u>ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ</u>***፡ "…. "በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ መሠፈርቶች ላይ የተመሠረተ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት በማቋቋም ረገድ የኢትዮጵያ መንግሥስትን እንዲደግፍ/እንዲያጠናክር"

# የቀጠለ

- ሁለቱ ተቋማት ባወጡት የጣምራ ምርመራ ሪፖርት ውስጥ የተዘረዘሩ ምክረ ሃሳቦች ጊዜውን በጠበቀ ውጤታማ፣ በተቀናጀ መልኩ እንዲፈፅሙ ለማድረግ የተለያዩ የምክክር መድረኮችን አዘጋጅተዋል።
  - ***ጥር 26 ቀን 2014 ዓ.ም***፣ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትን ጨምሮ የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰቡን፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን፣ ምሁራንን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቶ የነበረ ሲሆን፣ በመድረኩ ላይ የጋራ መግባባት ከተደረሰባቸው ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ዋነኞቹ ነበሩ ፣
    - በሽግግር ፍትህ ዙሪያ ከተለያይዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር ምክክር ማድረግ አስፈላጊነት፤
    - ወደፊት የሚደረጉ የሽግግር ፍትሕ ሂደቶችን አቅጣጫ ለማስያዝ የሚያግዝ ሰነድ ማዘጋጀት አስፈላጊነት።
  - ***ከመጋቢት 15 እስከ 16 ቀን 2014 ዓ.ም. በተዘጋጀ ሌላ የውይይት መድረክ ላይ***
    - በኢትዮጵያ ያሉትን ውስብስብ ችግሮችን ከመፍታት፣ ዘላቂ ሰላም እና ዕርቅን ከማስፈን፣ ተጠያቂነትን ከማረጋገጥ እና ለተጎጂዎች ተገቢውን መፍትሔ ከመስጠት አንፃር ሀገራዊ ዐውዱን ከግምት ውስጥ ያስገባ የሽግግር ፍትሕ ሂደትን ማስጀመር ተገቢነት እና ወቅታዊነት ላይ ሁሉም ተሳታፊዎች በአንድ ድምፅ ተስማምተዋል።

# የማኅበረሰብ ምክክሮቹ አላማዎች

- የሽግግር ፍትሕ ጽንሰሃሳቦችን እና ይህንን የፍትህ ሂደት ለማሳካት የሚያግዙ ስልቶችን/መንገዶችን በሚመለከት የአካባቢውን ማሕበረሰብ ግንዛቤ ማሳደግ፣

- እውነትን ከማውጣት፣ ተጠያቂነትን ከማስፈን፣ እርቅን ከማውረድ እና ተቋማዊ ማሻሻያዎችን ከማድረግ አንጻር  የተጎጂዎችን ምኞት እና ፍላጎት መለየት፣ መተንተን እና ወደፊት በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚነደፍ ማንኛውም አይነት የሽግግር የፍትህ ፕሮግራም/ፖሊሲ ግብዐት ሊሆኑ የሚችሉ ምክረ ሃሳቦችን መቅረጽ፣

- የሽግግር ፍትሕ ሂደቶችን የሚያግዙ ልዩ ማህበረሰባዊ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶችን፣ አካሄዶችን እና ጥሩ ልምዶችን መለየት እና መሰነድ።

# የማኅበረሰብ ምክክሮቹ አጠቃላይ ይዘት

| የመጀመሪያው እና የሁለተኛው ዙር ምክክሮች ከሐምሌ 2014 ዓ.ም. እስከ ታኅሣሥ 2015 ዓ.ም. ድረስ በ 13 የተለያዩ ቦታዎች ተከናውነዋል | |
|---|---|
| ምክክሮቹ የተደረጉባቸው ክልሎች | • አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሱማሌ እና ሐረሪ ክልሎች እንዲሁም የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር |
| የምክክሮቹ ተሳታፊዎች | • 435 ወንዶች እና 282 ሴቶች፣ በድምሩ 717 ግለሰቦች ተሳትፈዋል<br>• የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተጎጂዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦች፣ ተፈናቃዮች፣ የሃይማኖት እና የባህል መሪዎችን እና በሰብአዊ መብቶች እና በሰላም ግንባታ ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ የሲቪክ ማኅበራት ተውካዮች |
| የምክክር እና መረጃ አሰባሰብ ስነ ዘዴ | • እያንዳንዱ ምክክር ሁለት ቀናትን የሚውስድ ሲሆን ለግኝቶቹ መሰረት የሆኑት መረጃዎች እና ግብአቶች በተመጠኑ ቡድን ውይይቶች፣ ከዋና መድረክ በተንፀባረቁ ምልከታዎች እና በግል ቃለመጠይቆች አማካኝነት የተሰበሰቡ ናቸው<br>• ከ26 በላይ ሰቶች ብቻ የተሳተፉባቸው የተመጠኑ ቡድን ውይይቶች ተደርገዋል |
| ውስንነቶች | • በነሐሴ ወር 2014 ዓ.ም. በትግራይ ክልል ሊካሄዱ ታቅደው የነበሩ ሁለት ምክክሮች በአካባቢው የነበረው ግጭት በድጋሚ በመቀስቀሱ ምክንያት ለቀጣይ ዙር እንዲተላለፉ ተደርጓል። |

# የማኅበረሰብ ምክክሮቹ ዋና ዋና ግኝቶች

## 1) <u>ሰላም እና እና ደኅንነት</u>

- ተጎጂዎች ግጭቶች እና ከዚህ ቀደም ያጋጠሟቸው ጥሰቶች ያገረሻሉ በሚል የማያቋርጥ ሥጋት ውስጥ እየኖሩ እንደሆነ ገልጸዋል፤
- ሰላምና ደህንነት ማግኘት ቀዳሚ ፍላጎታቸው እንደሆነ እና ሌላው ሁሉ ነገር ቀጥሎ የሚመጣ መሆኑን
- በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የሚኖሩ እና የሚሠሩ ኢትዮጵያውያንን እኩል ጥበቃ ለማረጋገጥ ሕግን የማስከበር ሥራ እንደሚያስፈልግ
- በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚስተዋሉ ግጭቶች መነሻ ምክንያት ላይ ትኩረት በማድረግ መፍትሄ መቀየስ

# የማኅበረሰብ ምክክሮቹ ዋና ዋና ግኝቶች

## 2) ማካካሻን

- ከሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ ቀጥሎ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ተጎጂዎች ለደረሰባቸው ጉዳት ማካካሻ ማግኘት ነው፣
- ይህም ከግጭቱ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ፣ ካሳ፣ መልሶ ማቋቋም እና ጥሰቶቹ ወደፊት ላለመደገማቸው ዋስትና ማስቀመጥ ነው፣
- ተጎጂዎች የአጭር ጊዜ ፍላጎታቸው ምግብ፣ ውሃ፣ ንጽህና መጠበቂያ፣ መጠለያ እና የጤና አገልግሎት ያሉ መሠረታዊ አገልግሎቶች እንደሆነ በአንድ ድምጽ ገልጸዋል፤
- ተጎጂዎች ወደ ቀድሞ መኖሪያ ስፍራቸው መመለስ፣ ከፍርሃት ነጻ ሆነው መኖር እንዲችሉ ማድረግ፣ እና መተዳደሪያቸውን መልሰው እንዲያገኙ ማስቻል እንደሚያልፈልግ፣
- የማካካሻ ማእቀፎች ተጎጂዎች ወደ መደበኛ ሕይወታቸው እንዲመለሱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንዳለባቸው።

# እውነትን ማጣራት እና ማውጣት

- አደጋ ሊኖረው ቢችልም፣ እውነት የማፈላለግ አሰፈላጊነት እና በሂደቱ ተሳታፊ ለመሆን እንደሚፈልጉ
- እውነት የማፈላለግ ሂደትን መምራት ስላለበት አካል፡
  - ነጻ፣ ገለልተኛ፣ እምነት የሚጣልበት ራሱን የቻለ እውነትን ማጣራት እና ማውጣት ስልጣን ያለው ብሔራዊ ተቋም እንዲቋቋም
  - ሀቀኛ ባሕላዊ እና ሃይማኖታዊ መሪዎችን፣ ሴቶችን እና የተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎችን የሚወክሉ ሰዎችን ያካተተ
  - ባሕላዊ እና ሀይማኖታዊ መሪዎች በህብረተሰቡ መመረጥ እንዳለባቸው፣
  - ተአማኒነት እና ተቀባይነት እንዲኖር የአመራረጥ ሂደቱ ግልጽ፣አካታች እንዲሁም አቅም እና ችሎታን እንዲያገናዝብ

# እርቅና ሰላምን መፍጠር

- እርቅ እና ሰላም መፍጠር አሰፈላጊና የሚቻል ስለመሆኑ
- አስፈላጊ ከሆነ ይቅርታ ለመጠየቅ እና ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸው
- ይቅርታ እውነተኛ፣ ከልብ የመነጨ፣ እና ቀጥተኛ የይቅር በሉኝ ጥያቄን ከአስፈላጊው ካሳ ጋር መሆን እንዳለበት
- በአብዛኛው ሂደቱን ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ስርዓቶች አስፈላጊው ማሰተካከያ ተደርጎላቸው ቢመሩት ይመርጣሉ
- ጉዳታቸው በበዳዮች እና ተቋማት እውቅና ካገኘ፣ ተገቢው መፍትሄ ከተሰጠ፣ እንዲሁም ከፍተኛ የፌደራል እና ክልል ባለስልጣናት እና ሌሎች የታጠቁ ሀይሎች አዛዦች ይቅርታ ከጠየቁ ይቅር ይላሉ

# የወንጀል ምርመራ እና ተጠያቂነት

**የፍትህ ትርጉም**

- ተጠያቂነት፤ ላለፉ ግፎች እና የግጭት ታሪኮች መፍትሄ ማበጀት፤ ግጭቶች እንዲቆሙ እንዳይከሰቱ መከላከል፣ ተፈናቃችን ወደ በታቻው መመለስና መካስ፤

- **ተጠያቂ መሆን ያለባቸው አካላት**
  - በግጭት ወይም በሌሎች አውዶች ውስጥ ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች
  - ጥላቻን ያሰራጩ፣ ግጭቶችን የመሩ/የጠነሰሱ ሰዎች
- **ለተጠያቂነት ትኩረት የሚሹ ወንጀሎች**
  - እንደ አስገድዶ መድፈር እና ሲቪል ሰዎች መግደል አይነት ከባድ ወንጀሎች፤
  - ብሄርና ሃይማኖትን ተኮር ወንጀሎች
- **ፍትህ የሚያሰፍን አካል**
  - በመንግሥት ተቋማት በተለይም በሕግ አስከባሪ እና የዳኝነት አካላት ላይ ከባድ ቅሬታ መኖር
  - ነፃ እና ገለልተኛ መርማሪ እና ከሳሽ እንዲሁም ልዩ ፍርድ ቤት (ወይም ሀገራዊ ነፃ የሆኑ ልዩ ችሎቶች) ማቋቋም
  - የተወሰኑ ተሳታፊዎች፡ እርቅን ለማበረታታትም ሆነ ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለመከላከል መደበኛ ያልሆኑ (ባህላዊ/ሃይማኖታዊ አካሃዶች) መሻላቸው
- ነገር ግን የሴቶች ተሳትፎ ፤ አኩልነት፤ እና ሌሎች ሰብአዊ መብቶች መካተት እንዳለባቸው
- **ይቅርታና ምህረት**
  - ትዕዛዝ ከሰጡ አመራሮች እና ከባድ ወንጀል ከፈጸሙ ሰዎች ውጭ ያሉ

# ጥሰቶች እንዳይደገሙ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

- የሕግ የበላይነትን ማስከበር/  የሁሉንም ዜጎች ደህንነትን ማረጋገጥ፣
- ግጭቶችን እንዳይነሱ ለመከላከል ቀዳሚ መንገዶችን መቀየስ/መተግበር
- በመንግስትም ሆነ ከዚያ ውጭ ያሉ አጥፊዎችን ተጠያቂ ማድረግ
- በማኅበረሰቦች መካከል መከፋፈል እና መድሎን የሚያባብሱ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን ጨምሮ የህግና ተቋማዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ
- የሀይማኖት እና የማህበረሰብ መሪዎች ወጣቶችን ሥነ-ምግባር ማስተማር፣
- የመገናኛ ብዙኃን የተዛቡ መረጃዎች እና ጥላቻን/ ስሜትን የሚቀሰቅሱ ድርጊቶች መቆጠብ፣

# ትርጉም ያለው ተሳትፎ አስፈላጊነት

- በሽግግር ፍትህ ዙሪያ ማህበረሰብ አቀፍ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን፤
- በተለይም ግጭት ባለባቸው አካባቢ ያሉ ህዝቦች እና ተጎጂዎች ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልጋቸው፣
- ያቀረቧቸው ግብዐቶች የመንግስት ፖሊሲዎችን እና አሠራሮችን ለመቅረጽ እንዲያግዙ እና መልዕክቶቻቸው ፖሊሲ አውጪዎች ጋር እንዲደርስ፣
- በሽግግር ፍትህ ሂደት መሳተፍን ጨምሮ በመናገራቸው ምክንያት ጉዳት ይደርስብናል ብለው ሳይሰጉ ሃሳባቸውን የሚገልጹበት አስተማማኝ ምህዳር መፍጠር
- ካላቸው ልምድ አንጻር ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ መሪዎች በሽግግር ፍትህ ሂደቶች እና ስልቶች ውስጥ መሳተፍ እንዳለባቸው

# የሽግግር ፍትህ ትግበራ፣ ክትትል

- የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከጅምሩ እስከ መጨረሻው በገለልተኛ አካላት በየጊዜው ክትትክል ሊደረግበት እንደሚገባ
- የሽግግር ፍትህ ተቋማት በተሰጣቸው ተልዕኮ ላይ ምንም አይነት ጣልቃገብነት እንዳይኖር ክትትል ማድረግ
- አጠቃላይ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች የተዓማኒነት፣ ግልጽነት እና ሕጋዊነት/ተቀባይነት መስፈርቶችን እንዲያከብሩ
- አንዳንድ ተሳታፊዎች ያቀረቧቸውን ሃሳቦች የፖሊሲ አውጪዎች በምን መልኩ እንደተቀበሏቸው እና እንዳካተቷቸው ኢሰመኮ እና የተመድ ሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤት መረጃ እንዲሰጧቸው

# መደምደሚያ እና ጠቅላላ ምክረ ሃሳብ

- ለሽግግር ፍትህ ሂደት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፡ *የህግ የበላይነት፣ ሰላምና ደህንነትን ማስፈን እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንደይኖሩ መስራት*
- ዐውድ-ተኮር አካሄድን መከተል፣ ሃገራዊ ባለቤትነትን ማረጋገጥ
- አካታችና አሳታፊነት፣ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ተጎጂዎችንና የተለያዩ የማህበረሰብ አካላትን ያሳተፈ
- የፖሊሲ ዝግጂቱና የሽግግር ፍትህ ሂደቱ የሰብአዊ መብቶች መርሆችን ያከበረ ሊሆን እንደሚገባ

የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

United Nations
Human Rights

OFFICE OF THE HIGH COMMISSIONER FOR HUMAN RIGHTS